Amharic

# ልጄ ወደ ምውእለ ህፃናት ፕሮግራም ለምን አይሄድም?



በመጀመሪያ አመታት መማሩ ጠቃሚ ይሆናል። አንድ ልጅ ወደ ትምህርት፣ ሥራ ዓለም ሲገባና ሕይወቱን ሲጀምር ለውጥ ሊያምጣለት ይችላል። በመጀመሪያ አመታት በህጻኑ ላይ የሚከሰቱ ነገሮች በአንጎል እድገት ላይ ጫና ሊያስከትሉ ይችላል።

በቪክቶሪያ እያንዳንዱ ህጻን ለአንድ አመት የምውእለ ህጻናት እንዲያገኝ መንግሥት የገንዘብ እርዳታ ያቀርባል። ይህም ህጻኑ ት/ቤት ለመጀመረ አንድ አመት ሲቀረው ይሆናል።

የምውእለ ህጻናት ፕሮግራም በማህበረሰብ ምውእለ ህጻናት፣ በህጻን እንክብካቤ መስጫ ማእከል ወይም በአንዳንድ ት/ቤቶች ውስጥ መካሄድ ይችላል። የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ ምውእለ ህጻናት ሁሉም የምስክር ወረቀት ይለጥፋሉ (በወረቀት ግልባጩ ይመልከቱ)፣ እንዲሁም በሙያ የተካኑ የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ይኖራቸዋል።

## ከዚህ በበለጠ መረጃ

ለህጻናት በአካባቢያቸው ስለ የምውእለ ህጻናት ፕሮግራምና ሌሎች አገልግሎቶችን በተመለከተ በበለጠ መረጃ ከአካባቢዎ አስተዳደር ወይም ከአካባቢዎ ባለ የሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ ጽ/ቤት ለማግኘት ይቻላል። እንዲሁም ህጻናትን በተመለከተ በበለጠ መረጃ በመምሪያው ጽ/ቤት፣ የመጀመሪያ አመታት አገልግሎት ቅርንጫፍን በስልክ 1300 731 947 መደወል ወይም በድረገጽ by visiting the Department of Human Services website: **www.dhs.vic.gov.au/earlychildhood** ላይ የሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያን ማየት ይሆናል።

## ሰፋ ያለ ልምድ ተሞክሮ

የምውእለ ህጻናት ፕሮግራም ብዙ ዓይነት ልምዶችን ለልጅዎ ያቀርብለታል። ልጅዎ በሁሉም ምስኮች ትምህርቱን እንዲያዳብር ይህ ልምድ ይረዳዋል። አንዳንድ ሰዎች ይህ 'ለሁሉም ህጻን' ክትትል እንዲደረግ ያስገነዝባሉ።

ልጅዎ ከሚማረው ውስጥ አንዳንድ ሌሎች ነገሮች፡

- ቋንቋን መጠቀም
- ከሌሎች ጋር አብሮ መሆን
- በራስ መተማመን
- መሳል፣ ቀለም መቀባት፣ መዘመርና መደነስ
- መፍትሄ መፈለግ፣ መመራመርና ችግሮችን መፍታት ይሆናል።

ልጅዎ ስለሚከተሉት ይማራል

- እርሷ— ወይም እርሱ
- ሌሎች ሰዎችን
- ዓለም።

በተጨማሪም ልጅዎ ሙያዎችን ሲማርና መረጃዎችን ሲያገኝ፣ በበለጠ ጥሩ አንባቢና ጸሐፊ እንዲሆን ይረዳዋል።

## ከሌሎች ጋር አብሮ ስለመማር

ልጅዎ ከሌሎቹ ህጻናት ጋር እንዴት አብሮ መማር እንዳለበት ሲያውቅ ይህም

- ተንከባካቢና ለሌሎች ደግ መሆን
- ስለማይወዱት ሰው አወንታዊ ምላሽ መስጠት
- ስሜትን በጥሩ መንገድ ማሳየት
- ሌሎችን መርዳትና ከሌሎች እርዳታ ማግኘት
- ችግርን ለመፍታት ጥሩ መንገዶችን መማር
- ነገሮችን ለማስፈጸም ከሌሎች ጋር አብሮ መሥራት ይሆናል።

## ስለ እያንዳንዱ ህጻን

የልጅነት አስተማሪው ልጅዎን በቅድሚያ ያውቀዋል። ከዚያም እርስዎንና ቤተሰብዎን በማወቅ ስለ እርስዎ ባህልና ማህበረሰብ ያውቃል/ታውቃለች። አስተማሪው የልጅዎን ጥንካሬ፣ ፍላጎቶችና ችሎታ ለማወቅ ይችላል። ልጅዎ እንደሌሎቹ ሳይሆን እንደ ልዩ ሰው ይታያል።

## ስለድጋፍ ሰጭ ወላጆች

ከሌሎች ወላጆች ጋር ለመተዋወቅ እድል ይኖርዎታል። ስለልጅዎ የሚያሳስብ ጉዳይ ሲኖር ከአስተማሪው ጋር በመነጋገር እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። ልጅዎ ምን እንዲሆን እንደፈለጉና እንዴት እንደሚከታተሉት ለሠራተኞች በማሳወቅ ታዲያ ልጅዎ በምውእለ ህጻናት ውስጥ በተሻለ ማካሄድ ይችላል።

እንዲሁም ልጅዎ ተጨማሪ እርዳታ ካስፈለገው በምውእለ ህጻናት በኩል እርዳታ እንዲያገኝ ይደረጋል። የምውእለ ህጻናት ፕሮግራም ከሌላ ዓይነት እርዳታ ጋር የተቀናጀ ነው። ለልጅዎ ወይም ለርስዎ ሌላ አገልግሎት ካስፈለገ የምውእለ ህጻናት ሠራተኛ ሊረዳዎት ይችላል።

## ስለወደፊት ማሰብ

በምውእለ ህጻናት ፕሮግራም ውስጥ ያሉ በአብዛኞቹ በሚቀጥለው አመት ት/ቤት ይጀምራሉ። ታዲያ የሚቀጥለውን እርምጃ በጥሩ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ የምውእለ ህጻናት ሊረዳ ይችላል። ህጻናት በራሳቸው ከተማመኑ የሚያጋጥማቸውን ሁኔታ በሚገባ ሊወጡት ይችላሉ። ለህጻናትና ቤተሰቦች በቀላሉ ት/ቤት እንዲጀምሩ ለመርዳት የምውእለ ህጻናት ፕሮግራም ያላቸው ብዙ አገልግሎቶች ከአካባቢ ት/ቤት ጋር ይሠራሉ።

**የህጻናት ጽ/ቤት…ህጻናት ጥሩ ኑሮን እንዲጀምሩ ለቪክቶሪያ ቤተሰብ ይረዳሉ**

A Victorian Government initiative

Victoria The Place To Be

Department of Human Services

This document is managed by the Department of Education and Early Childhood Development, Victoria (as of 27 August 2007)

# የምውእለ ህጻናት ምስክር ወረቀት




አራት አመት እድሜ ላለው ልጅዎ የምውእለ ህጻናት ወይም የህጻን መንከባከቢያ ፕሮግራም ሲያማርጡ ይህንን የምስክር ወረቀት መመልከት ይሆናል።

The Kindergarten Certificate፡ ማለት የምውእለ ህጻናት አገልግሎት በሙያ የተካኑ የልጅነት ጊዜ አስተማሪ የሚካሄድና በግዛት መስተዳድሩ በኩል የገንዘብ እርዳታ የሚያገኝ ነው። የመጀመሪያ አመታትን ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዱ ህጻን ለአንድ አመት የምውእለ ህጻናት መንግሥት የገንዘብ እርዳታ ይሰጣል። አብዛኛው ህጻኑ ት/ቤት ለመጀመር ከአንድ አመት በፊት ነው።

## ለበለጠ መረጃ

በአካባቢዎ ሰለሚገኝ ምውእለ ህጻናት ፕሮግራሞች ለበለጠ ማብራሪያ ከአካባቢዎ አስተዳደር ጋር በሚከተለው ድረገጽ ላይ መመልከት:

**www.mav.asn.au/**

**www.vicnet.net.au/government/localgovt**

የመጀመሪያ አመታት የህጻናት ጽ/ቤትን በድረገጽ — **www.dhs.vic.gov.au/earlychildhood** ማየት ይሆናል።

ወይም ለህጻናት የመጀመሪያ አመታት አገልግሎት ሰጪ ቅርንጫፍን በስልክ 1300 731 947 (በአካባቢ ሂሳብ) ደውሎ ማነጋገር ይሆናል።

A Victorian Government initiative

Victoria The Place To Be

Department of Human Services